የአክሱም ሐውልትና የጣሊያን
መንግስት ቅንነት ማጣት
ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት

በሮም የሚገኘው የአክሱም ሐውልት በ4ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ አክሱማዊው መንግስት ክርስትናን ከመቀበሉ ጥቂት ቀደም ብሎ ከተሰሩት ታላላቅ ሐውልቶች የሚበልጠው ትልቁ ሐውልት ነው። ሐውልቱ በአሠራሩ ረቂቅነት ለጥንታዊ ኢትዮጵያዊያን ቴክንካዊ ብቃት ምስክር በመሆን ለአለፉትም ሆነ ለመጪ ትውልድ ኢትዮጵያውያንና አፍሪካዊያን ኩራት ሆኖ ይኖራል።

በሮም ያለው ሐውልት በቀድሞ ሥፍራው ተመልሶ በዚያ ከሚገኙ የአክሱም ሐውልቶች ጋር አብሮ እስካልቆመ ድረስ የታሪካዊ ቅርሶቹ ሁኔታ ያልተሟላ ይሆናል።

የሐውልቱ ዝርፊያ በ/1937/

በፋሽስታዊው አምባገነን መሪ ቤኒቶ ሙሶሎኒ ትእዛዝ ሐውልቱ ከታሪካዊ ስፍራው በዝርፊያ ተነቅሎ የተወሰደው በ1937 እ.ኤ.አ.ሲሆን በዚሁ ዓመት ኦክቶበር28 ቀንበሮማ ከተማ አደባባይ እንዲቆም ተደረገ። ይህ ዕለት/ኦክቶበር 28/የተመረጠው ሙሶለኒ በ1922 የጣሊያንን ዲሞክራሲ ያስወገደበትንና «ማርች ኦን ሮም» በመባል የሚታወቀውን ዕለት 15ኛ ዓመት ለማክበር ተብሎ ነበር።

እውነተኛ ዲሞክራት ጣሊያኖች ይህንን የነፃነታቸውን መደፈር የዲሞክራሲን መደመሰስ ለመዘከር ታስቦ በዋና ከተማቸው አደባባይ እንዲተከል የተደረገውን የተሰረቀ ሐውልት በማየት ደስታን ያገኙበታል የሚል እምነት የለንም። አምባገነኑ መሪ ሙሶሎኒ መንግስቱን «በበሰበሰው የጣሊያን ዲሞክራሲ ሬሳ ላይ» እንደገነባ በመግለፅ ሲደነፉ እንደነበርም የሚዘነጋ አይደለም።

የዓፄ ኃ/ሥላሴ ተቃውሞ

የአክሱም ሐውልት መዘረፍ መጀመሪያ ተቃውሞ የገጠመው በዚያው በተወሰደበት ዓመት 1937 ዓ.ም. ነበር። ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ባደረጉት ንግግር የሐውልቱን መወሰድ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በፋሽስቶች ከተፈፀመበት በደል አንዱ አድርገው ዘርዝረውታል። ይህንንም <ህይወቴና የኢትዮጵያ ርምጃ> በተሰኘው መፅሃፋቸው ክፍል ሁለት ተፅፎ ይገኛል።

በ1947 የጣሊያን የሰላም ውል ታሪካዊ
ቅርሶችና ቅኝ ግዛቶች

በ1947 ጣሊያን ከተባበሩት መንግስታት ጋራ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በተፈራረመችው ውል አንቀፅ 37 ላይ «በ18 ወራት ጊዜ ውስጥ ጣሊያን ከኦክቶበር3/1935 ጀምሮ ከኢትዮጵያ ምድር የተወሰዱ የሥነጥበብ ሥራዎች፤ ሃይማኖታዊ ዕቃዎች፤ መዛግብትና ማንኛውንም ታሪካዊ ዋጋ ያለው ቅርስ ለኢትዮጵያ ወይም ለሕዝቦቿ እንድትመልስ...» ተዋውላለች። /ኦክቶበር 3 1935 ጣሊያን ኢትዮጵያን በግፍ የወረረችበት ጊዜ ነው/ ይህ ውል እስከ ዛሬ ድረስ ያልተመለሰውን የአክሱምን ሐውልት ለመመለስ ግዴታ ያልተወጣው በመዘንጋት ነው ወይስ ቅንነት ጎድሎት ? የሚለውን ጥያቄ ለማንሳት እንገደዳለን።

ይህንን ጥያቄ ከመመለስ በፊት ውል ውስጥ የተካተቱ ሌሎች ነጥቦችንም ማየት ተገቢ ይሆናል።

የዚህ ውል ዋናውና በጣም አስፈላጊ ፍሬ ነገር ኢጣሊያ በአፍሪካ የነበራትን ቅኝ ግዛቶች የይገባኛል ጥያቄ ዳግመኛ እንዳታነሳ ለማረጋገጥ ሲሆን፤ በእርግጥ ግን የይገባኛል ጥያቄውን ዳግመኛ አላነሳም ማለቷ ቀናነትን የተላበሰ ነበር ወይ ?ብለን እንድንጠይቅ ይገፋፉናል። ውሉ በተፈፀመበት ዕለት የኢጣሊያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለተባበሩት መንግስታት ተፈራራሚ ኀይሎች በላኩት ማስታወሻ ላይ «ለኢጣሊያ ህዝብ ያላቸውን

አመለካከት እንደገና እንዲመረምሩ» ጠይቀዋቸዋል። በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ደግሞ የኢጣሊያ ዲፕሎማቶች ሲሯሯጥበት የነበረው ጉዳይ ኢጣሊያ ወደ አፍሪካ እንድትመለስ ለማድረግ ሲሆን በዚህም የደቡብ አሜሪካ ካቶሊክ አገሮችን ድጋፍ አግኝተው ነበር። ይህም ኢጣሊያኖቹ ቅኝ ግዛቶቻቸውን በተመለከተ ዳግመኛ ጥያቄ አናነሳም የማለታቸው ነገር በእርግጥ ከልብ እንዳልነበር በግልፅ ያሳያል።

የዶንጎ ንብረቶች

በአፕሪል 1944 ዓ.ም. ሙሶሎኒ በስዊስ ድንበር አጠገብ ዶንጎ ላይ በኢጣሊያን አርበኞች ሲያዝ በእጁ 3 የኢትዮጵያ ንጉሣዊ ዘውዶች ተገኝተዋል። ምናልባትም ከደብረሊባኖስ ገዳም የተዘረፉ ሳይሆኑ አይቀሩም። ዘውዶቹ በወቅቱ ፎቶግራፍ ተነስተው ፎቶግራፉቸው በተለያዩ ጊዜያት ለህትመት የበቃ ሲሆን በተለይም ኢፓካ የተባለው የጣሊያን ጋዜጣ የኦገስት 25/1968 ዕትምን መጥቀስ ይቻላል። በኋላ በኢጣሊያን አገር «ጠፉ» ተብሎ የተወራባቸው እነዚሁ ንጉሳዊ ዘውዶች ወደ ኢትዮጵያ ሳይመለሱ ቀርተዋል። ይህም የተደረገውን ስምምነት በመፃ ረር ነው። ፎቶግራፎቹ ከተነሱ በኋላ ዘውዶቹ በእርግጥ «ጠፍተው» ከሆነ የኢጣሊያን መንግስት ክብሩንና ስሙን የሚጠብቅ ቢሆን ሌላው ቢቀር በጉዳዩ ሊያዝንና ሊፀፀት ይገባው ነበር። በእርግጥ ውሉን የሚያከብር ቢሆን ኖሮ በውስጡ የተጠቃለሉት አንቀፆች በሚሉት መሰረት የተረፉትንና «ያልጠፉትን» ንብረቶች ለመመለስ አስቸኳይ እርምጃ ይወስድ ነበር። በትክክል የሆነውን ግን አብረን እንመልከት።

የይሁዳ አንበሳ ሐውልት

ወደ ሮም ከተወሰዱ ቅርሶቻችን አንዱ የይሁዳ አንበሳ ሐውልት ሲሆን ይህም በሙሶሎኒ ትዕዛዝ ከአዲስ አበባ ተወስዶ በጣሊያን ዋና ከተማ እንዲተከል ተደርጓል። የኢጣሊያን መንግስት ይህንን ሐውልት ለመመለስ በመቻኮል እርምጃ ለመውሰድና «የጠፉትን» ዘውዶች ለመደባበቅ ያደረገው ሙከራ ምን ይመስል ነበር ? የዚህን መልስ በቅርቡ ለህትመት የበቃውና በክቡር አቶ አማኑኤል አብርሃም የተፃፈው «ሪመኒሰንሰስ ኦፍ ማይ ላይፍ» የተባለው የህይወት ታሪካቸውን ያካተተው መፅሃፍ ይዞ ወጥቷል። ከ1952-1955 እ.ኤ.አ. በኢጣሊያ የኢትዮጵያ መንግስት አምባሳደር ሆነው በሠሩበት ጊዜ ለኢጣሊያን ባለስልጣኖች ጉዳዩን አንስተውባቸው ነበር።የተሰጣቸው መልስ ሐውልቱ «ሊገኝ አልቻለም» የሚል ነበር። አልፎ ተርፎም አንድ የጣሊያን ባለሥልጣን «የኢትዮጵያ መንግስት ሌላ ሐውልት ቢያሰራ ይሻለዋል» ብሎ እስከማፌዝም ደርሷል። አቶ አማኑኤል ባደረጉት ክትትል እንደደረሱበት ሐውልቱ ከሙሶሎኒ ውድቀት በኋላ በባለቃልኪዳኖቹ አገሮች ኮሚሽን ቁጥጥር ሥር እንደነበረና የኢጣሊያ መንግስትም ስለ ሐውልቱ መገኛ ለኮሚሽኑ የቀረበውን ጥያቄ ለመከታተል አልተጨነቀበትም። የኢጣሊያ መንግስት በተከታዩ ወቅት የሐውልቱን «መጥፋት» በድጋሚ ሲገልፅላቸው አቶ አማኑኤል የሰጡት ምላሽ «በደምብ ብትፈልጉት ታገኙታላችሁ» የሚል ነበር። ለአምባሰደሩ ምስጋና ይግባቸውና በመጨረሻ ሐውልቱ «ተገኘ» ተብሎ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ከተደረገ በኋላ ከፋሽስት ወረራ በፊት በነበረበት የቀድሞ ቦታው ተተክሎ አዲስ አበባ የባቡር ጣቢያ ፊት ለፊት የሚገኘውን አደባባይ አስውቦት ይገኛል።

የአክሱም ሐውልት ጥያቄ

አሁን «ጠፋ» ተብሎ ለመደበቅ የማይቻለውን የአክሱም ሐውልት ጥያቄ እናነሳለን። አቶ አማኑኤል የይሁዳ አንበሳውን ጥያቄ ባቀረቡበት ወቅት ስለ አክሱሙም ሐውልት ጉዳይ አንስተው ነበር። የኢጣሊያ መንግስት ቀናነት ቢኖረው ኖሮ ጥያቄውን በወዳጅነት መንፈስ ተቀብሎ ትብብር ሊያደርግና ይልቁንም በውል የገባውን ግዴታ ሊያከብረው ይገባ ነበር። አቶ አማኑኤል እንደሚተርኩልን ሲኞር ሜንዶላ የተባሉት የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ጄኔራል ዳይሬክተር «ከአንድ ደቂቃ ላላነሰ ጊዜ መሬት መሬት እያዩ ከቆዩ በኋላ አንዲት ቃል እንኳን መተንፈስ ሳይችሉ ቀርተዋል።»

ሌላው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣን ደግሞ ሐውልቱ በዚያው በሮማ ሊቀር እንደሚገባው አስተያየታቸውን ከሰጡ በኋላ «ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰጠ ስጦታ» ተብሎ

የሚነበብ ማስታወሻ ከበስተጎኑ በኩል ሻጥ ቢደረግበት እንደማይከፋ ያለ ዕፍረት ተናግረዋል።

ሁሉም እንደሚያውቀው ሐውልቱ በስጦታ የተሰጠ ፈፅሞ አይደለም። ፋሽስታዊ ወረራ በሰጣቸው ጊዜያዊ ድል ተዘርፎ የተወሰደ እንጂ፤ ወረራው በወቅቱ ዓለምን ያስደነገጠ፤ በ50 የመንግስታት ማህበር አባላት የተወገዘ በዓለም ሕግ በተከለከለ የሙስታርድ ጋዝ ጭፍጨፋ የታገዘ፤ የግፍ ወረራ ነበር። ወረራው የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል አምቡላንሶችንና ሆስፒታሎችን ሆን ተብሎ በቦንብ ያቃጠለ፤ እጃቸውን የሰጡ እስረኞችን በጥይት የደበደበ፤ አቡነ ጴጥሮስን የመሰሉ አባት በግፍ እንዲገደሉ ያደረገ፤ የየካቲት አስራ ሁለቱን የግራዚያኒን በሺህዎች የሚቆጠሩ ንፁሐን ዜጎችን ጭፍጨፋ ጨምሮ የደብረ ሊባኖስ መነኮሳትን ያስረሸነ፤ የግፍ ወረራ ሲሆን ለዚህ ሁሉ ተደራራቢ ወንጀል የኢጣሊያን መንግስት እስከዛሬ ድረስ ይቅርታ አልጠየቀም።

ከጦርነቱ በኋላ የተቋቋመው የኢጣሊያ መንግስት ፋሽስት ባይሆንም ከፋሽዝም ቅሪት በሙሉ የተላቀቀ መሆኑን ለመመስከር አስቸጋሪ ይሆናል። ምስክሩም ከኢትዮጵያ በፋሽ-ስቶች የተዘረፈውን ንብረት በእጁ ማቆየቱ ነው። በኢትዮጵያ ከሙሶሎኒ ውድቀት በኋላ የኢትዮጵያ ጠ/ሚኒስትር ሆኖ የተሾመው ሌላ ሳይሆን ፔትሪዮ ባዶሊዮ ነበር። ባዶሊዮ በኢትዮጵያ የዘመተው ጦር አዛዥ ሆኖ በመርዝ ጋዝ ለተደረገው ጭፍጨፋ ለቀይ መስቀል አምቡላንሶችና ሆስፒታሎች የቦምብ ድብደባ ተጠያቂ የነበረ የኢጣሊያ ማርሻል እንደነበር ከአእምሮአችን የሚወጣ አይደለም። በተጨማሪ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደጎርፍ ለፈሰሰው ደም ተጠያቂ ከሆኑት ሰው እንኳን በኢትዮጵያ ለፈፀመው ወንጀል ተጠያቂ ሆኖ ለፍርድ አልቀረበም።

አቶ አማኑኤል በአንድ አጋጣሚ ለጣሊያኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ካርዲዮ ስለ አክሱም ሐውልት አንስተው ሲናገሩ «በርካታ ጣሊያናውያን ያላስተዋሉት ነገር ቢኖር የአክሱም ሐውልት በኢትዮጵያውያን ዘንድ የሚታየው እንደ አንድ የተቀረፀ ድንጋይ ሳይሆን የ2ሺህ ዘመን ታሪክ ቅሪት በመሆኑ በምንም ነገር ሊለወጥ የማይችል መሆኑን ነው» ብለው ነበር።